# ስለ ዝውውር ማወቅ ያለብዎት

## የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች




**ማስታወሻ።** ይህ በራሪ ወረቀት ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነ መረጃን ይዟል። ያልተረዱት ነገር ካለ፣ አንድ ባለሥልጣን እንዲያስረዳዎት መጠየቅ ይችላሉ።

AMHARIC

# ይዘት


ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው? 3

ከተመረጡ ወደ የትኛው አገር ይዛወራሉ? 4

ለመዘዋወር ከተመረጡ ምን ይጠበቅብዎታል? 5

ከባለሥልጣናት ጋር መተባበር ካልቻሉ ምን ይከሰታል? 5

ከእርስዎ ጋር የቤተሰብ አባላት ካሉዎትስ? 6

ከመዛወርዎ በፊት ቃለ መጠይቅ ይደረጋል? 6

የዝውውር ውሳኔውን ካልተቀበሉ ምን ማድረግ ይችላሉ? 7

- ለእግድ ተፈጻሚነት እና ተከታይ ይግባኝ አንድ ላይ ይግባኝ ማለት 8

የዝውውር ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? 9

ከተዛወሩ በኋላ ምን ይከሰታል? 10

## ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው?

በአውሮፓ ህብረት ውስጥ ያሉ አገራት እና ሌሎች ተጨማሪ 4 አገራት የስደተኞች እና የፍልሰት አስተዳደር ደንብ (Asylum and Migration Management Regulation፣ AMMR) የተባለ የጋራ ህግ ላይ ተስማምተዋል። ይህ ህግ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻን የመመርመር ሃላፊነት ከነዚህ አገራት መካከል የማን እንደሆነ ለመወሰን ይረዳል። እነዚህ አገራት የአውሮፓ ህብረት+ (EU+) አገራት ይባላሉ።



አንድ አገር ብዙ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎች በአንድ ጊዜ ከተቀበለ እና ሊያስተናግዳቸው ካልቻለ፣ ሌሎች አገራት በተለያዩ መንገዶች ሊረዱት ይችላሉ። አንዳንድ አመልካቾች ወደ ሌላ አገር ሊዛወሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ዝውውር ይባላል።

ይህ ሁኔታ ከተከሰተ፣ የእርስዎ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በዚህ አገር ላይ ላይመረመር ይችላል። በአሁኑ ጊዜ 26 የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገራት ብቻ ወደ ሌሎች አገራት በዝውውር ሊሳተፉ ይችላሉ።

**አስፈላጊ! አሁን በላትቪያ ውስጥ ነው ያሉት፣ የአውሮፓ ህብረት+ አባል አገር ናት።**

በአሁኑ ጊዜ በዝውውር ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ 26 የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገሮች የሚከተሉት ናቸው፡ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ቼክያ፣ ጀርመን፣ ኢስቶኒያ፣ አይርላንድ፣ ግሪክ፣ ስፔን፣ ፈረንሳይ፣ ክሮኤሺያ፣ ጣሊያን፣ ሳይፕረስ፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ሃንጋሪ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ኦስትሪያ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሮማኒያ፣ ስሎቬኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ፊንላንድ እና ስዊድን።

በአሁኑ ጊዜ በዝውውር ላይ የማይሳተፉት 5ቱ "ተባባሪ" አገሮች እና ሌሎች አገሮች የሚከተሉት ናቸው፡ ዴንማርክ፣ አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ እና ስዊዘርላንድ።

## ከተመረጡ ወደ የትኛው አገር ይዛወራሉ?

ማን ሊዛወር እንደሚችል ባለሥልጣናት ይወስናሉ።

በመጀመሪያ፣ ከሌላ አገር ጋር **ጠንካራ ግንኙነት** እንዳለዎት ያጣራሉ። እነዚህ ግንኙነቶች በሚከተሉት ላይ ሊመሰረቱ ይችላሉ፡

- የቤተሰብ ጉዳዮች (ቅርብ የቤተሰብ አባላት ብቻ ሳይሆኑ እንደ የአጎት/የአክስት ልጆች ያሉ የሰፊ ቤተሰብ አባላትም ጭምር)
- የባህል ጉዳዮች (ለምሳሌ የዚያን አገር ቋንቋ መናገር ከቻሉ)

**አስፈላጊ!** ወደ የትኛው አገር እንደሚዛወሩ መምረጥ አይችሉም።

ከሌላ አገር ጋር ግንኙነትዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ካሉዎት፣ ወዲያውኑ ለባለሥልጣናት ማቅረብ አለብዎት። ያለበለዚያ ባለሥልጣናት ግንኙነትዎን ከግምት ውስጥ ማስገባት አይችሉም።

ይህ ግን ወደዚያ አገር እንደሚዛወሩ ዋስትና አይሰጥም።



ከሌላ አገር ጋር ምንም ዓይነት ጠንካራ ግንኙነት ከሌለዎት፣ በዝውውር ላይ በተሳተፉት አገሮች በሚወሰን አገር ውስጥ ይመደባሉ።

## ለመዘዋወር ከተመረጡ ምን ይጠበቅብዎታል?



ለመዘዋወር ከተመረጡ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡

- ከባለሥልጣናት ጋር መተባበር እና መመሪያዎቻቸውን መከተል
- የጉዞዎ ቀን እስኪደርስ ድረስ በዚህ አገር ውስጥ መቆየት እና ባለሥልጣናት እርስዎን ሊያገኙዎት መቻል አለባቸው
- ማመልከቻዎ እስኪመረመር ድረስ በሚዛወሩበት አገር ውስጥ መቆየት።

## ከባለሥልጣናት ጋር መተባበር ካልቻሉ ምን ይከሰታል?

**አስፈላጊ!** ከባለሥልጣናት ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ ይህ በእርስዎ ላይ አሉታዊ መዘዞችን ያስከትላል።

ያለ ባለሥልጣናት ፈቃድ ወደ ሌላ አገር ከተጓዙ ወይም ከተዛወሩበት አገር ከወጡ፣ እንደ አመልካችነት ያለዎትን የተወሰኑ መብቶች ያጣሉ። ለምሳሌ፡-

- **በርካታ የድጋፍ ዓይነቶች እና አገልግሎቶችን አያገኙም።**
- **ስራ እንዲሠሩ** ወይም ኮርሶችን እንዲከታተሉ አይፈቀድልዎትም።



## የዝውውር ውሳኔውን ካልተቀበሉ ምን ማድረግ ይችላሉ?

በአሁኑ ጊዜ የቅርብ ቤተሰብዎ አባላት አብረውት ከሆኑ እና ለመዘዋወር ከተመረጡ፣ ቤተሰብዎ ከእርስዎ ጋር አብሮ ይዛወራል።

ቅርብ የቤተሰብ አባላት ተብለው የሚታሰቡት:-



- ባለቤትሽ ወይም ሚስትህ
- የተረጋጋ ግንኙነት ያለዎት ግን ያላገቡት አጋርዎ



- ልጅዎ (ከ18 ዓመት በታች እና ያላገባ) ናቸው።

## ከመዛወርዎ በፊት ቃለ መጠይቅ ይደረጋል?



ከእርስዎ ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ቃለ መጠይቅ ይዘጋጃል። ይሄም በደህንነት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። እንዲህ ላለው ቃለ መጠይቅ መሄድ ካለብዎ፣ ባለሥልጣናቱ አስቀድመው ዝርዝር መረጃ ይሰጡዎታል።

## የዝውውር ውሳኔውን ካልተቀበሉ ምን ማድረግ ይችላሉ?



ለመዘዋወር ከተፈቀደልዎ፣ ወደ የትኛው አገር እንደሚዛወሩ የሚገልጽ **የዝውውር ውሳኔ** ይሰጥዎታል።

በዝውውር ውሳኔው ካልተስማሙ፣ ምክንያቶችዎን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ይግባኝ ማቅረብ ይባላል። ውሳኔውን ይግባኝ ሲሉ፣ ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ሰጪ አካል የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል።




ከፈለጉ በይግባኙ ላይ፣ የሕግ አማካሪ እና አስተርጓሚ ያለክፍያ ሊረዱዎት ይችላሉ።

የዝውውር ውሳኔውን ለመቃወም (ይግባኝ ለማለት) ሦስት ምክንያቶች ብቻ አሉ፦

- ወደዚያ የተመረጠ አገር መዘዋወርዎ የሰብአዊ መብቶችዎን ይቃረናል ብለው ከተከራከሩ።
- በዝውውሩ ውሳኔ ጊዜ ያልነበረ ነገር ግን ውሳኔውን ሊለውጠው የሚችል አዲስ መረጃ ሲኖር።
- በሌላ አገር ውስጥ ቤተሰብ ካለዎት እና በምትኩ ከእነሱ ጋር መገናኘት ካለብዎት።

ወደ ሌላ ሀገር ለመዘዋወር በተላለፈው ውሳኔ ላይ ካልተስማሙ፣ ያንን ውሳኔ በፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይኖርብዎታል።

## ለእግድ ተፈጻሚነት እና ተከታይ ይግባኝ አንድ ላይ ይግባኝ ማለት

የዝውውር ውሳኔው በሚሰጥዎ ጊዜ ይግባኝ ለማቅረብ ያለው የጊዜ ገደብ፣ የት እና እንዴት እንደሚሆን ይብራራል።

ወደ ሌላ አገር እንዲዘዋወሩ ከውሳኔው ጋር የማይስማሙበትን ምክንያት(ዎች) መስጠት አለብዎት።

ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ ወደሚዛወሩበት አገር ለምን መዛወር እንደሌለብዎት ምክንያትዎን ወይም ምክንያቶችዎን መስጠት አለብዎት።

ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ ይግባኝዎ እየተካሄደ እያለ በዚህ አገር ውስጥ ውሳኔውን መጠበቅ ይችሉ እንደሆነ **በ1 ወር** ጊዜ ውስጥ ይወስናል። ይህ የእግድ ተፈጻሚነትን ይግባኝ በመባል ይታወቃል።

ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ በዚህ አገር ውስጥ ሆነው ውጤቱን መጠበቅ እንደማይችሉ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፣ ወደሚዛወሩበት አገር ይተላለፋሉ።

ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ በዚህ አገር ውስጥ እንዲቆዩ ሊፈቀድልዎ እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፣ ፍርድ ቤቱ የዝውውር ውሳኔው ከመታገዱ ጋር በተያያዘ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 1 ወር ውስጥ ወደሚዛወሩበት አገር መዛወር እንዳለብዎት ወይም እንደሌለብዎት የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ይሞክራል።

ይግባኝዎ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወዳለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ይዘዋወራሉ። ዝውውሩ የሚከናወነው ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔውን ካደረገበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ በ 4 ሳምንታት ውስጥ ይሆናል።

**አስፈላጊ!** ከባለሥልጣናት ጋር መተባበር እና ወደሚዛወሩበት አገር መጓዝ አለብዎት።

## የዝውውር ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?




ውሳኔውን ካልተቃወሙ፣ ዝውውሩ የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ በ4 ሳምንታት ውስጥ መከናወን አለበት።

ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ በዚህ አገር እንዲቆዩ የሚያስችል ምንም ምክንያት እንደሌለ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፣ ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ ወደሚዛወሩበት አገር ይተላለፋሉ።

የዝውውር ውሳኔውን ከተቃወሙ እና ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ በዚህ አገር እንዲቆዩ ሊፈቀድሎት እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፣ ይግባኙ ውድቅ ከተደረገ፣ ዝውውሩ በይግባኝ ውሳኔው በ4 ሳምንታት ውስጥ መከናወን አለበት። ከመዘዋወርዎ ቀን በፊት ቢያንስ 2 ቀናት ቀድሞ ይነገራችኋል። ይግባኝዎ ተቀባይነት ካገኘ፣ አይዛወሩም እና በዚህ አገር ውስጥ ይቆያሉ።

ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ በዚህ አገር እንዲቆዩ የሚያስችል ምንም ምክንያት እንደሌለ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፣ ይግባኝዎ በመታየት ላይ እያለ ወደሚዛወሩበት አገር ይተላለፋሉ።

## ከተዛወሩ በኋላ ምን ይከሰታል?

በተለምዶ፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻ በሚዛወሩበት አገር ይመረመራል። ከተዛወሩ በኋላ በሌላ አገር ውስጥ የቤተሰብ አባል እንዳለዎት ከተረጋገጠ፣ ማመልከቻዎን ለመመርመር ወደዚያ አገር ሊተላለፉ ይችላሉ።

ይህ በራሪ ወረቀት ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደው ለኢ.ዩ. አባል ሀገራት ብቻ ነው። የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ በራሪ ጽሑፍ ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይቀበልም። በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025